# የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)

**Ethiopian People's Congress for United Struggle (Shengo)**

www.ethioshengo.org shengo.derbiaber@gmail.com


ሰኔ 28፣ 2008 (ጁላይ 5፣ 2016)

## የመብት ማስከበር ትግሉ ተጠናክሮ ይቀጥላል

የስርአቱ ጸጥታ ሀይሎችና ባለስላጣኖች ባለፈው እሁድ ሰኔ 26፣ 2016 ሰማያዊ ፓርቲ በባህርዳር ለማካሄድ ያቀደውን ህዝባዊ ስበሰባ በመከልከል ለዚሁ ስራ ተሰማርተው የነበሩትን የፓርቲው የህግ ክፍል ሀላፊና የስራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባል የሆኑት አቶ አዲሱ ጌታነህ፣ ሌሎች የድርጅቱን አባላትና የባህር ዳር አደራጆችን እንዲሁም ለዚሁ ስራ የሚያገለግለውን መኪና ሺፌርረዳት ሳይቀር ባጠቃላይ አስራአንድ ሰዋች በማሰር የታቀደው የህዝብ ስብሰባ እንዳይሳካ አድርጓል።

ይህ የስርአቱ ህገወጥ ተግባር አሁንም ቢሆን መሰረታዊ የኢትዮጵያ ህዝብ መብት ለማክበር ምንም ፍላጎት እንደሌለው በድጋሚ የሚያረጋግጥ ነው። እጅግ የሚገርመው ደግሞ ይህን ቀጣይ የመብት ረገጣ የሚያካሂደው የአቶ ሀይለማርያም ደሳለኝ መንግስት መልካም አስተዳደርና የህዝብን መብት ለማክበር እንደሚሰራ ደጋግሞ በሚለፍፍበት ሰአት መሆኑ ጭምር ነው።

የዚህ አይነቱ ቀጣይ የመብት ረገጣ አሁንም በፍጥነት እየተወሳሰበ የመጣውን የሀገራችንን ቀጣይ ችግሮች እጅግ ያወሳስቡታል፣ የህዝቡንም ቁጣ እጅግ ያባብሱታል የነጻነት ፍላጎትና ቁርጠኛነቱንም እጅግ ያጠናክረዋል እንጂ ከቶውንም ሊገድለው አይችልም።

የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ የታሰሩት የሰማየዊ ፓርቲ አመራሮች፣ አደራጆችና ሰራተኞች እንዲሁም ሌሎች የፖለቲካ እስረኞች ባስቸኳይ እንዲፈቱ ፤ ስርአቱ ከዘህ የተሰላቸና የከሸፈ ኋላቀር የመብት ረገጣ ተላቆ የኢትዮጵያን ህዝብ መሰረታዊ መብት ያለማመናታት እንዲያከብር አሁንም ያሳሰባል:፡ ይህ ደግሞ የመደራጀት፣ የመሰብሰብ፣ ሀሳብን በነጻ የመግለጽና ሌሎች መሰረታዊ መብቶችን ያጠቃልላል።

ሁሉም ኢትዮጵያዊ ይህ አስከፊ የጭቆና ስርአት እንዲያከትም በምትኩም ህገመንግስታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እውን እንዲሆን ከተቃዋሚዎች ጎን በመቆም መብቱን ለማስከበር ትግሉን አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!


Tel: 44 7937600756 , +1 9168486790 E-mail : shengo.derbiaber@gmail.com